ከዝሁር በፊት አራት ረከዓዎች ላይና ከዝሁር በኋላ አራት ረከዓዎች ላይ የተጠባበቀ ሰው አላህ እሳትን በርሱ ላይ እርም አድርጎለታል።

የነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ባለቤት ከሆነችው ከኡሙ ሐቢባ (ረዲየሏሁ ዐንሃ)
- አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው እንዲህ አለች: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: "ከዝሁር በፊት አራት ረከዓዎች ላይና ከዝሁር በኋላ አራት ረከዓዎች ላይ የተጠባበቀ ሰው አላህ እሳትን በርሱ ላይ እርም አድርጎለታል።"» [رواه أبو داود والترمذي والنسائي وابن ماجه وأحمد] [ነው። ሶሒሕ[

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከዝሁር ሶላት በፊት አራት ረከዓ ሱና ሶላቶችን፣ ከዝሁር በኋላም አራት ረከዓ ሱና ሶላቶችን የሰገደ፣ የዘወተረና የተጠባበቀን ሰው አላህ በርሱ ላይ እሳትን እርም እንደሚያደርግ አበሰሩ።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/11251